# በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም
## (ለማኅበረ ቅዱሳን)

ራሱን ማህበረ ቅዱሳን እያለ የሚያሞካሽው ድርጅትን አስመልክቶ አዲስ አበባ የሚገኙት ህገወጡ ፓትርያርክ በሚመሩት ስብሰባ ላይ የመወያያ ርዕስ ሆኖ ማህበሩ ጽንፈኛና አልፎም ሽብርተኛ የመሆን አዝማሚያ እንዳለው ሲናገሩ በተለያዩ የሶሻል ሚዲያ ላይ ተመልክተናል። የማህበሩ አባላት ደግሞ ሰሞኑን በሀሰት ተወነጀልን ፓትርያርኩን ሊያስወግዙን በማለት የድረሱልን ጥሪ በነጻውና በገዢው መንግስት ተቃማዊ ሚዲያ ላይ እያስተጋቡ ይገኛሉ። አልፎ ተርፎም ማህበራችው ላይ እርምጃ ከተወሰደ ቤተክርስቲያኗ አደጋ ላይ እንደምትወድቅም እያሰፈራሩንም ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚታገለው የአንድነት ኃይል ይህና ዜና እንዴት ያስተናግደው ለሚለው ጥያቄ የማኅበረ ቅዱሳን ጉዞ መመርመር ግድ ይላል።

***ለመሆኑ ማህበረ ቅዱሳን ማን ነው?***

የኢቲዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የቅርብ ጊዜ ታሪክን ላልተከታተለ ሰው «ማህበረ ቅዱሳን» በዘመነ ወያኔ የተፈጠረ ይመስለዋል። ሆኖም ግን የቤተክርስቲያኗን ታሪክ ጠንቅቀው የሚያቁ ይህ ቡድን ወደ ዝዋይ ወርዶ ባገኘው በክርስትና ስሙ «ማህበረ ቅዱሳን» ሳይሆን አዳፋ ታሪክ ባለው በቀድሞ ስሙ «አጠቃላይ ጉባኤ» በሚለው ነው። የቤተክርስቲያኗ ህጋዊ ልሳን የሆነው ዜና ቤተክርስቲያን በሚያዝያ 1996 እትሙ «ማህበረ ቅዱሳን» እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

«ማኅበረ ቅዱሳን አሁን የሚጠራበትን የክርስትና ስም ወደ ዝዋይ ወርዶ ሳያገኝ ምን ዓይነት ስመ ተጸውኦ እንደነበረው አሁን እንኳን ያሉት የማኅበሩ አባላት ሊያቁት አይችልም። የሁለተኛውን ፓትርያርክ (አቡነ ቴዎፍሉስን) አባትነት ላለመቀበልና አላማችውን ለማደናቀፍ አጠቃላይ ጉባኤ በሚል ስም የተቋቋመ ነበር።»

በወቅቱ የአጠቃላይ ጉባኤ የቤተክርስቲኗን ወጣቶች በሙሉ የመቆጣጠር የመመልመል እንዲሁም አባል የማድረግ አልፎም በመዋጮ መልክ ከአባላቱ አስራት የመሰብሰብ ስልጣን እንዲሰጠው ይህንንም ሲያደርግ ቤተክርስቲያኗ ምንም ዓይነት ቁጥጥር እንዳታደርግበት እንደፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ አቡነ ቴዎፍሎስ ውድቅ ስላደረጉበት እነ አጠቃላይ ጉባኤ ወይም በክርስትና ስማቸው ማኅበረ ቅዱሳን አቡነ ቴዎፍሎስን ለመቃወም በሃይማኖት መሪ ላይ የሞት ፍርድ ወስነው ለገዳዮች አሳልፈው ሰጡ። በወቅቱ የነበሩት የሲኖዶስ አባላት ቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ የፈጸሙትን እኩይ ድርጊት ስለሚያውቁ «የአጠቃላይ ጉባኤ» ማለትም «ማኅበረ ቅዱሳን» በቤተክርስቲያን ውስጥ ማኅበር ለሟቋቋም የሚያደርገው እንቅስቃሴ በአሰቸኳይ እንዲቆም በማድረግ ከቤተክርስቲያን መድረኮች እንዲገለል ውሳኔ አስተላለፉ። የአቡነ ቴዎፍሎስ ደቀመዝሙር ነኝ የሚሉትም አቡነ ጳውሎስ ይህን ሁሉ እያወቁ ማኅበሩ በስደት የሚገኙትን አባቶች ስለሚዘልፉና ስለሚያሳድዱላቸው ቤተክርስቲያኗን እንዲቆጣጠሩ ፈቀዱላቸው። ላለፉት 20 ዓመታት ማኅበሩ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ስንመለከት የ0ርባ ዓመት የቤተክርስቲያን የመቆጣጠር ምኞቱ እንደተሳካለት እናያለን። ማኅበሩን የአጠቃላይ ጉባኤ መስራቾች በጀርባ እንደሚመሩት የዚህ ማኅበር አፈ ቀላጤ የነበረው ዳንኤል ክብረት ከማህበሩ ሲገለል በእንቁ ጋዜጣና (ጁላይ 2011 እትም) በደጀ ሰላም ድረ ገጽ ላይ በጻፈው መልእክቱ ማኅበሩን የሚመራ ስውር የአመራር አካል እንዳለ ጠቁሟል።

**የወያኔና የማኅበረ ቅዱሳን ጊዜያዊ የጥቅም ጋብቻ**

ወያኔ ስልጣን በጨበጠ ማግስት በቤተክህነት ከታዩት ነገሮች አንዱ የቀድሞው «አጠቃላይ ጉባኤ» በአዲስ ስም «ማኅበረ ቅዱሳን ብሎ ብቅ ማለቱ ነበር። ገዢው መንግስት ቤተክህነቱን ለማዳከም ማኅበረ ቅዱሳንን እንደመሳሪያ ሊጠቀምበት ስለፈለገው የወያኔ/ኢሕአዴግ 5ኛ ረድፍና መንፈሳዊ ክንፍ ሆኖ እንዳሻው የሚንቀሳቀስ ብቸኛ ማኅበር እንዲሆን ፈቀደለት። በወቅቱ የማኅበሩ እንቅስቃሴ ሕልውና እንዳይኖረው የተከለከለበት ቦታ ቢኖር የትግራይ ክልል ብቻ ነበር። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መንገድ «ማኅበረ ቅዱሳን» በህገወጡ ሲኖዶስ እውቅና አግኝቶ ቤተክርስቲያኗ ያላትን የሰንበት ት/ቤት ለመምራት ከአባላቱም አስራት በኩራት እንዲሰበስብ ኮንትራት ተቀበለ ነገር ግን ሀብቱም ሆነ እንቅስቃሴው በቤተክርስቲያን ውስጥ ያይደለ ማኅበር እንዲሆን ተፈቀደለት። ለሰብዓዊ መብት ለፍትህ የሚታገሉ ወጣቶችን በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋሚት ተማሪዎችን ወደማኅበሩ ከመለመለ በኋላ «ማኅበራችንን በማናችውም የፖሊቲካ እንቅስቃሴ ስለማይገባ ማኅበራችንን እንዳታስመቱ ወያኔ ላይ የተቋውሞ ድምጽ አታሰሙ» በማለት የወጣቶችን በተለይም የሕዝባዊ የትግል ፊታውራሪ የሆነውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትግል እንቅስቃሴ ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሶበታል።ወያኔ ደግሞ በተራው ለማኅበረ ቅዱሳን የገንዘብና የስልጣን እርዳታ በማድረግ ወሮታውን ከፍሏል።

በዚህ ዓላማ መሰረት ነው፤ ማህበሩ ላለፉት ዓመታት 20 ዓመታት መፈንቅለ ፓትርያርኩን ተቃውመው «ሲኖዶሱ የወንበዴዎች ዋሻ ሆነ» ብለው የተሰደዱትን አባቶች ላይ የጭቃ ጅራፉን ሲዘረጋ በአንጻሩ አባ ጳውሎስን የማህበሩ ልሳን በሆኑት የስምዓ «ጽድቅ» ጋዜጣና የሐመር መጽሔት ሲያወድስ ኖራል። ይኸው ማህበር የብዙዎች ኦርቶዶክሳውያን ደም በእጁ ላይ የሚገኝ፣ ብዙዎችን ወጣቶችን አሳዶ ለፕሮቴስታንት አዳራሽ የመገበና በስደት ላይ የሚገኙትን አባቶች ለሞትና ለእስራት የሚመኝ ድርጅት ነው። በስምዓ ሀሰት ጋዜጣው ላይ የተሰደዱትን አባቶች ለምን አልሞቱም ለምንስ ተሰደዱ በማለትም ሲያንጎራጉር ከርሟል። ህገወጡ ሲኖዶስ በአባይ ጸሃይና በታምራት ላይኔ እርዳታ መንበረ ፓትርያርኩን በሃይል ከነጠቀ በኋላ በውጭው ዓለም እንዳሰቡት ተቀባይነት ስሳሳገኙ ማህበረ ቅዱሳን እና የስልጣን ጾር ያለባቸውን ደካማ ካህናት በመሳሪያነት በመጠቀም ስደተኛውን ህዝብ ለመከፋፈል ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። የወያኔ ዓላማ

የሚያከናውኑባቸው አብያተ ክርስቲያናትንም በውጭው አለም አቁመዋል። በመቀጠልም  የሰኞን ውዳሴ ማርያም ያልዘለቀው ግን እራሱን ዲያቆን/መምህር/የታሪክ ተመራማሪ እያለ የሚጠራው የማህበረ ቅዱሳኑ ዳንኤል ክብረትና የማህበሩ ጋሻ ጃግሬዎች እንደዚሁም  ከወያኔው የክርስትና አባት ከአባ ማትያስ ጋር በመሆን በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች እየተዘዋወሩ «ትክክለኛው ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ ናቸው፤ በአቡነ ጳውሎስ  የሚመራው ቤ/ክ ስር ካልታቀፋችሁ ጥምቀታችሁ ጥምቀት ቁርባናችሁ ቁርባን አይደለም» እያሉ በመስበክ ህዝቡን ለመከፋፈል ያልተሳኩ ሙከራዎችን አድርገዋል። የቤተክርስቲያኑን የእውቀት ውቅያኖስ ጨልፈው የጨረሱ የመሰላቸው የማህበረ ቅዱሳን አመራር አካላት እራሳቸውን ከልጅነት እስከ እውቀት በሽምግልና በስደት ህዝባቸውንና አገራቸውን ካገለገሉ አባቶች ጋር ማስተካከላቸው በራሱ አስገራሚ ነው። በሰደት የሚገኙት የህጋዊ ሲኖዶስ አባላት ወያኔ ቤተክርስቲያንን እንዳይደፍር የታገሉ፣ የጮሁና በመጨረሻም ሰሚ ሲያጡና በወያኔ ለግድያና ለዕስራት ሲፈለጉ የእመቤታችንን፣የሐዋርያትን በስተኋላም የሊቃውንቱን  የእነ ቅዱስ አትናቴዎስን ፈለግ፤ ከሁሉም በላይ የባለቤቱን «ከአንዱ ሀገር ሲያሳድዱአችሁ ወደ ሌላው ሂዱ» የሚለውን አምላካዊ ቃል ተከትለው የተሰደዱ አባቶች ናቸው። እነዚህን አባቶች ማህበረ ቅዱሳን የተሀድሶ ስም ታርጋ እየለጠፈባቸው በአገልግሎታቸው የማሰናከያ ድንጋይ ሲቆልል ከርሟል። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፦ በቴክሳስ፣ በዋሽንግተን ሲያትል፣በዴንቨር፣ በካሊፎርኒያ ኦክላንድና ሎስ አንጀለስ፣ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በኒውዮርክ፣ በጂዮርጂያ አትላንታ እና በሌሎች ከተሞችና አህጉሮች ጭራሽ ለቤተክርስቲያን እንግዳ በሆነ መልኩ የወንጌል ጉባኤን በጩኸት መረበሽ፣ ፓትርያርክ መርቆሬዎስ ላይ ወደ አትላንታ ገብርኤል ክብረ በዓል እንዳይገኙ ጸባቴ የማነ ከሚባል ካህን ጋር የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄድ፣ የታላቁ ቅዱስ  አባት ብጹእ አቡነ ዜና የባረኩትን ጉባኤ ማወክ አልፎም ረግጦ መውጣት፣ በስደት የሚገኙ ታላላቅ አባቶችና የወንጌል ሰባኪዎችን በሐሰት ስም የሚያጠፋ ወረቀት በቤተክርስቲያን አካባቢ መበተንና  በምእመናን መካከል አሉባልታ በመንዛት በስደት የሚገኙትን አባቶች እንዳይቀበሉ ሞክሯል። በስደት ያለችውን ቤተክርስቲያንና በስደት ሆኖ የሀገሩን ናፍቆት በሆዶ አምቆ የባእዳንን ኑሮ ኑሮዬ ብሎ ያለውን ህዝበ ክርስቲያን ለማሸበርና ለመከፋፈል መሰመሩን በተቀናጀ መልክ ዘርግቶ ነበር። እንደ አገር ቤት ማስደብደብና ማስገደል ባይችልም በትምህርታችው ምእመናንን ከመናፍቃን መንጋጋ ያስጣሉ ሰባክያነ ወንጌል ካህናትን ጳጳሳትን ሳይቀር የመናፍቅነት ስም በመስጠት በስደት የሚገኙ ወጣቶችን ከሚወዱአችው ካህናት ለመለየት ያደረገው ጥረት በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች ከፍተኛ ተቋውሞ ገጥሞት ከሽፏል። በስደታቸው እንኳን በሰላም እንዳይቀመጡ በህጋዊ ሲኖዶስ አባላት ላይ ይህን  ሁሉ ጥቃት ያካሄደው ሀገር ውስጥና በውጭ ዓለም የሚገኙት አባቶች መለያየት  ለማህበሩ ያስገኘውን የንግድ ጥቅም ዓይነተኛ ምክንያት ነው። ለዚህም ነው በአባቶች መካከል የተከሰተውን የአስተዳደር/የቀኖና ልዩነት  የሃይማኖት እንዲሆን ከፍና ዝቅ ብለው  እነዚህ አባቶች እንዲወጋገዙ ትልቅ መሳሪያ በመሆን ከሜድሮክና ከኤፈርት ቀጥለው በኢትዮጵያ ውስጥ የወጣላቸው ታክስ የማይከፍሉ የንግድ ድርጅት በመሆን ተጠቅመዋል። ሰለሆነም ቤተክርስቲኗን በመከፋፈል የራሳችውን ህልውና በማስፋፋት የማህበሩን መሪዎች በገንዘብ ለማበልጸግ የዘመናዊ መኪናዎችና የትላልቅ ህንጻ ባለቤቶች መሆን ችለዋል።

በሀገር ውስጥ የዚህ ድርጅት አካሄድ ያሰጋችው የተዋህዶ ልጆች ቤተክህነት የማኅበሩን እንቅስቃሴ መሰመር እንዲያስዝ በተለያየ ጊዜያት ጩኸት ቢያሰሙም  ሰሚ አልተገኘም። ይባስ ብሎ ብጹአን አባቶች ተሰደው ቤተክርስቲያና ለሁለት በመከፈልዋ ግራ የተጋባውን ህዝበ ክርስቲያን የበለጠ  ግራ እያጋባ፤በስልጣኑ መንገድ ላይ የቆሙትን በማስገደልና በማስደብደብ ካልተቻለም የመናፍቅነት ካባ በማልበስና ስም በማጥፋት ከቤተክርስቲያን እንዲባረሩ በማድረግ ለመናፍቃን ሲሳይ ዳርጓል። በሀገር ቤት ያሉ ሊቃውንት በዚህ ማህበር የአሉባልታና የሐሜት መሳሪያ በሆነው ጋዜጣና መጽሔት ላለመዘለፍና  በአባላቱ ላለመድበደብ ፈርተው አፋችውን ሸብበው ከርመው አሁን በግልጽ መናገር መድፈራችውና መጀመራችው ቤተክርስቲያና ወደ ቀደመ ክብራ የመመለስ የመጀመሪያ ምእራፍ የተከፈተ ይመስላል። ለማንኛውም የማኅበሩ እኩይ አካሄድ የቤተክርስቲያኗን አንድነትና እድገት እንደ ቅዠት ለሚያስፈራው ወያኔ፤ አማራንና የኦርቶዶክስና አከርካሪ መምታት በአጀንዳነት ቀርጾ ለመጣው ወያኔ በማገልገል ተልዕኮውን ፈጽሟል። ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ ጥሩ አድርጎ ተጠቅሞ መምታት የሚያቅበት ወያኔ ይህንን ድርጅት ጨዋታው አለቀ ዳቦ ተቆረሰ ማለቱን እየሰማን ነው። **<u>ለማንኛውም ሕገ ወጡ ፓትርያርክ  አቡነ ማትያስ ይህንን የታሪክ አጋጣሚ ተጠቅመው ማኅበር ቅዱሳንን መስመር ካስያዙ የበደሏትን ቤተክርስቲያን እንደሚክሱ የተዋህዶ ልጆች ሙሉ እምነት ነው።</u>**

**የማኅበረ ቅዱሳንና የወያኔ የጥቅም ጋብቻ ፍቺ**

ድሮም ሌባ ሲሰርቅ ሳይሆን ሲካፈል እንሚጣላው የወያኔና የማኅበረ ቅዱሳን ችግር ይኸው ነው። በመሰረቱ ማኅበሩ መንፈሳዊነት የጎደለው የንግድና የፖሎቲካ ድርጀት በመሆኑ ቤተክርስቲያና የማታውቀውና ያልመዘገብችው ንብረትና ገንዘብ ማህበሩ በግለሰብ ስም የባንክ የባንክ አካውንት ያንቀሳቅሳል በተጨማሪም የንግድ ቤቶችና የብዙ አክሲዮን ባለቤቶች ሆነዋል። በገዳማት ስም ፕሮጀክት እየቀረጹም ዶላር በአካፋ እየሰበሰቡ ለገዳማት በማንኪያ ይሰጣሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን ያለምንም ተጠያቂነትና ግልጽነት ነው። ለዚህም ነው የገዳማት አበው በስማችን መነገድ ይብቃ የሚል ድምጽ ያሰሙት። ከምንግዜም በላይ የወያኔ ባለልስጣናት በአሁኑ ሰዓት የንግድ ስራ ላይ ስለተሰማሩ ከማህበሩ ጋር በመስመር ላይ ስለተጋጩ ነው ጋብቻው በፍቺ ያለቀው። ማህበረ ቅዱሳን በህልውና የሚመጡበትን አባቶች በገበሬ አስደንግጥ ስያሜው ተኃድሶ፣መናፍቅና ቀሳጭ እንደሚለው ወያኔም የአይኑ ቀለም ያላማረውን አካል የአሸባሪነት ታርጋ እንደሚለጥፈው የቅዱሳኑን ማህበር አሸባሪውና ጽንፈኛ  ቡድን ብሎት በአየር ላይ አንሳፎታል። **በሰፈሩት ቁና መሰፈር ማለት ይሄ ነው።**

የማህበረ ቅዱሳን አፈ ቀላጤዎች  በብርሃን ፍጥነት የሰብዓዊ መብት ታጋዮች ሆነው ሰሞኑን የመንግስት ተቃማዊ ድረ ገጾች ላይ ወያኔን በትንሹም ቢሆን ለኮፍ እያረጉ ነው። ለመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን የምርጫ 97ትን አስከትሎ በተፈጠረው ረብሻ የወያኔ አጋዚዎችን  አዲስ አበባ ነዋሪዎችን በአልሞ ተኳሽ መሳሪያ የህጻን ነቢዩ፣የሽብሬና የሉሎች ጭንቅላት ሲያፈርስ ትንፍሽ ብሏል? ምእመናኑ  በምህላ ጸሉት አምላካችውን በቤተክርስቲያን ተሰባስበው እንዳይማጸኑ አባ ጳውሎስ ሲከለክሉ እርሳቸውን ቅዱስነታቸው እያለ በማሞካሸት ከመተባበር በቀር ተቋውሞ አሰምቷል? አባ ጳውሎስ ባህታዊውን በአደባባይ ሲያስገድሉ ማኅበሩ የት ነበረ? አባ ጳውሎስ የምህረት አደባባይ ከሆነችው የቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ከወያኔ ወታደር ሸሽተው የገቡትን ተማሪዎች አሳልፈው ሲሰጡ ማኅበሩ ትንፍሽ ብሏል። ይልቁንም በሰደት ያለውን ሕዝብ ለመከፋፈል አባትነታችውን ተቀብሎ እየተባረከ በኃዘኑ እየተጽናናባቸው በመከራ ጊዜ ድምጽ የሆነለትን ህጋዊውን ሲኖዶስ አባላትን ስም በማጥፋት ዘመቻ ላይ ነበረ። እንዲያውም በስደት የሚገኙት አባቶች ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን አፋናና የሰብዓዊ መብት ለማስተጋባት ከህዝቡ ጎን ቆመው በአደባባይ የሚያሰሙትን ጩኸት ለማጣጣል እንደዚሁም በስደት ላይ የሚገኘው  ምእመን  አደባባይ ወጥቶ  ድምጹ የታፈነውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይስተጋባ የማህበሩ «ሊቆች» ባገኙት የቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ሁሉ «ክርስቲያን ድምጹን የሚያሰማው በጸሎት እንጂ በሰላማዊ ሰልፍ አይደለም» በማለት ሲማጸዱቅና ሲተቹ ተሰምተዋል እግረ መንገዳቸውም የአንድነት ኃይሎችን ትግል የማዳከም ስልት ነበር ። እነዚህ በቤተክርስቲያናችን ረጅም ታሪክ ሂደት ምንም ስፍራ የሌላቸው ጉዶች የሳቱት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በታሪኩዋ በሀገር ጉዳይ ላይ እንግዳና ተመልካች ሆና አታውቅም። እንዲያውም ቀዳሚ ሆና ታወያያለች፣ታታግላለች ለነፃነታቸው ደማቸው እንዲያፈሱ ህዝቦቻን በአንድነት ታስነሳለች። ለዚህም ነው የፋሺስት ኢጣሊያና የሀገር በቀሉ ጠላት የወያኔ ኢላማ የሆነችው። ለማንኛውም የዚህ ማኅበር ትጋት አንድና አንድ ነው፤ይኸውም የቤተክርስቲኗን ስልጣንና ገንዘብ መቆጣጠር።

**የማኅበረ ቅዱሳን ስውሩ ዓላማ**

ዋና ዓላማው የቤተክርስቲያኗን የስልጣን መዋቅር መቆጣጠርና ቢጽ ሀሳዊና የባልቴቶች ተረት የሆነው ትምህርታቸውን ማሰራጨት እንደዚሁም የአመራር አባላቱን ተጠቃሚ ማድረግ ነው። በተለይም የግብጽ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ፖፕ ሺኖዳ ከሰንበት ትምህርት ቤት የወጡ ናቸው በሚል ዘይቤ የጵጵስናውንና የፓትርያርክነቱን ስልጣን የማህበሩ አባላት አንድ ቀን መያዝ ረጅሙ እቅዳቸው ነው። ይህንን ለመጸፈም ለአላማው ደጋፊ የሆኑት ጳጳሳትን ያለምንም መመዘኛ ማስሾም እንደዚሁም ምንም  የቤተክርስቲያንዋ ትምህርት የሌላችውንም በቅስና በዲቁና ያሾማሉ። በተጨማሪም በቤተክህነት ውስጥ ያሉ የተለያዩ መምሪያ ሃላፊዎችና ጳጳሳትን ጨምሮ ከማኅበረ ቅዱሳን የደሞዝ ፔይሮል ላይ በማስቀመጥ አጀንዳቸውን ያስፈጽማሉ። ይህን ስውር ዓላማችውን የተገነዘበው የዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ከላይ በተጠቀሰው እትም እንዲህ ብሉ አግራሞቱን ገልጾታል።«ቅዱስ መጽሀፍ በአባቶችሽ ፈንታ በአባቶችሽ እግር በአባቶችሽ ምትክ ልጆች ተወለዱልሽ ተተኩልሽ አለ እንጅ አባታቸውን አጥፍተው ልጆች ተወለዱልሽ አላለም ወላጆቻቸውን ገድለው የተወለዱ አርዊ ገሞራዊት ልጆች ብቻ ናችው አባቱን የሰለበ እናቱን ያገባና ጌታውን የሸጠም የአስቆሩቱ ይሁዳ ብቻ ነው። »

**መልእክት ለመላው ኦርቶዶክሳውያን እንዲሁም ለአንድነት ኃይሎች**

በቅዱሳን ጸሎት በአበው ትምህርት በሰማዕታት ደም ጸንታ የኖረችው ኦርቶዶስሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችንን ድርጅት/የጽዋ ማኅበር አይተካትም በድርጅትም አትመራም። የምትመራው በመንፈስ ቅዱስ እርሱ አድሮበት በሚመራው በህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። <u>ሆኖም ወያኔን ጥግ አርጎ መፈንቅለ ሲኖዶስ አካሂዶ መንበሩን በኃይል የተቆጣጠረው ሕገ ወጡ ሲኖዶስና ፓትርያርክ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ እዚህ ድርጅት ላይ እርምጃ ቢወስድ የተከፈለችውን ቤተክርስቲያናችንን አንድ የማድረግ ጥርጊያ መንገድ እየከፈተ መሆኑን ተገንዝበን ህገ ወጡ ሲኖዶስ ወደ ልቡ ለመመለስ የመጀሪያውን ምዕራፍ በመከፈት ላይ መሆኑን አሰተውለን ስለ ቤተክርስቲያናችን አንድነት ስንል በደስታ ልንቀበለው ይገባል።</u>

በግብዞች የተሞላው የቅዱሳኑ ማኅበር ምን ያህል ግብዝ እንደሆነ ለማሳየት በዘሃበሻ ድረ ገጽ የማህበሩ «ሊቀ ሊቃውንት» ዳንኤል ክብረት ያለውን እስቲ እንየው

« ቤተ ክርስቲያን እንወክላለን የሚሉ ሰዎች ናቸው ሰሞኑን ተሰብስበው ተከሳሹ በሌለበት ፍርድ ሲሰጡ ያየናቸው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ተሳሳተ ተብሎ እንኳን ቢሆን ቤተ ክርስቲያኒቱ ለአርዮስና ለንስጥሮስ፣ ለመቅዶንዮስና ለሰባልዮስ የሰጠችውን መብት ቤተ ክህነቱ ለማኅበረ ቅዱሳን ሊነፍገው አይገባም ነበር»

ዳንኤል  ከውሎ አበል የተረፈውን ዶላር ባለማወራረዱ  ከአመራር ጋር በተፈጠረው አተካራና ግጭት ከማህበሩ ቢለቅም ለበላችበት እንደምትጮኸው እንሰሳ በፍጹም ግብዝነት እየጮኸ ይገኛል። እስቲ ዳንኤል ጥያቄ እንጠይቀው፡- ለመሆኑ እድሜ ልካቸውን ቤተክርስቲያን ያገለገሉ የ89 ዓመቱን አዛውንት አያሌ ሊቃውንት ያፈለቁ ታላቅ አባት  ብዛት ያላቸውን መጻህፍት ጽፈው ለቤተክርስቲያኗ ያበረከቱን ታታሪ አባት ብጹእ አቡነ መልከጼዴቅን በዛ አዘጋጅ በነብርክበት የስማዕ ሃሰት ጋዜጣው መናፍቅ ብለብ በጨዋው እውቀትህ ስትከስና ስትፈርዳባቸው አሁን ለማቅ ይሰጠው ያልከውን መብት አግኝተው ነበር። በዛ የአሉባልታህ ጋዜጣ ላይ ቤተክርስቲያኗ አለኝ ከምትላችው ታላላቅ ት/ቤት ተምረው የወጡና መሉ ህይወታችውን በሐዋርያነት  ለወንጌል የሰጡ ታላላቅ ሰባኪያንን ስማችውን ስታስጠፋ ለማቅ ይሰጥ የሚለውን እድል ሰጥተህ ነበር። **በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም።** ለነገሩ ከቤተክርስቲያናችን የትምህርት ውቅያኖስ ተካፋይ ለመሆን እድሉ ስላልገጠመህ ለምን ብለህ እድሉን እትሰጣለህ።  የሰኞን ውዳሴን ማርያምን ላልዘለቀ  የድቁናን ስም ተሸክሞ ተንስኡ በሎ ላልጮኸ ከዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ዲግሪ ለተመረቀ ግለሰብ ዘለፋው ይቀላል። ውድ ኦርቶዶክሳውያን ዶላር ለጥቂት መሪዎቻቸው

ለመሰብሰብ የሚሮጡ በቤተክርስቲያን ስም የሚነግዱ፤ የቤተክርስቲያን ልጆችን እንደማስተማር የደከሙትን መክሮ እንደ መሰብሰብ ጥላሸት እየቀቡ የመናፍቅነት ካባ እየደረቡ ማባረር የተዋህዶ ልጅነት መለኪያ አይደለም እንዲያውም ለኦርቶዶክስ ምዕመን ቁጥር ማሽቆልቆል ይሄ ድርጅት የአንበሳ ድርሻ ይወስዳል። የተዋህዶ ልጆች ጸሎትና እንቅስቃሴ ሊሆን የሚገባው አባቶቻችን አንድ እንዲሆኑልን ነው። ይሄ ድርጅት እያለ ደግሞ አባቶቻችን አንድ አይሆኑም ያለፈውም እርቅ እንዲፋረስ ያደረገው አባይ ጸሃይን ጨምሮ የማቅ ንስሐ አባት የሆኑት አቡነ ሳሙኤልና የማህበሩ አመራር አባላት እንደነበሩ የቅርብ ገዜ ትዝታችን ነው። ሌላው በውጭ ያሉ አብያተክርስቲያናት ልብ ሊሉ ሊጠነቀቁ የሚገባችው ነገር ቢኖር ማቅ የጥፋት ስልቱን ቀይሯል። በሃገር ውስጥ ከወያኔ የነበራቸው ጋብቻ እያለቀ መሆኑን ስለተገነዘቡ የማህበሩ የቀድሞ አመራራሮች እነ በላቸው፣ብርሀኑ ጎበና፣የሃመሩ ያሬድና እነ ኤፍሬም ቀድመው ወደ ሀገረ አሜሪካ መጥተዋል። ሜይ 2014 ውስጥ ቺካጎ ላይ ላይ ባደረጉት 16ኛው ዙር የማኅበሩ ስብሰባ ዋሽንግተን ዲሲ የማህበሩን ህንጻ ሊገዛ እንደበፊቱ በሰደት የሚገኘውን ሲኖዶስ በአደባባይ ሳይሳደቡ እንቀብላለን የሚሉ አፈ ጮሌ ካህናት  ውጭ ሀገር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሰርጎ በማስገባት ህዝቡ አሰባስበው ህንጻ አሳንጸው በቀናነት ሲያገለግሉ የቆዩ አባቶችን  ከህዝቡ ጋር አለያይተው  በመጨረሻም ወደራሳቸው ጎራ ለመቀላቀል የሚያስችል ስልት ነድፈው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ይህም ክስተት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያን ብልጭታው እየታየ ነው።

በመጨረሻም የዳንኤል ክብረት ጽሁፍ እንደዚሁም የማህበሩ ልሳናት ቤተክርስቲያኗ እንደተመዘበረች፣ ስለ መልካም አስተዳደር እጦት እንዲሁም የቤተክርስቲያን አባቶች እየተያዙ ለእስራትና ለሞት ተዳረጉ ይሉናል።ጥያቄው እነማን ናቸው ለዚህ ያበቁዋት ነው። ገዳይና አልቃሽ አንድ ሲሆኑ በጣም ነው የሚገርመው። የቆሙትን እየገደሉ ለሞቱት ማልቀስ ግብዝነት ነው። ጌታ ለእንዲህ ዓይነቱ ትውልድ እንዲህ ይላል «የነቢያትን መቃብር የምታንጹ የጻድቃንን መቃብር የምታስጌጡ እናንተ ግብዞች ወዮላችሁ።በአባቶቻችን ዘመን ኑረንስ ቢሆን የነቢያትን ደም ለማፍሰስ ከእነርሱ ጋር አንድ ባልሆንም ነበር ትላላችሁ። ነቢያትን ለገደሉ ሰዎች ልጆቻችሁ እነሆ ትመስክራላችሁ። እናንተም የቀረውን ፈጽሙ።» (ማቴ 23፥29-32)

ዛሬ ማህበሩ እንደሚኩራራው ሳይሆን የኦርቶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታችን የማንንም ድርጅት እገዛ ሳትፈልግ ብዙ ማእበላትን አልፋለች። ጉዲት፤ግራኝ ፣ዘመነ መሳፍንትና፣የፋሺስት ኢጣሊያ ዘመንን አሳልፋለች። ወያኔም ያልፋል። በነዚያም ወቅቶች እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያናቸው የተዋደቁት አባቶችና እናቶች በትህትና «የማንጠቅም ባሪያዎች ነን። ልናደርግ የሚገባንን ያደረገነው» አሉ እንጂ በድፍረት ማህበረ ቅዱሳን ባይኖር ኖሮ ቤተክርስቲያኗ አደጋ ላይ ትወድቃለች አላሉም።

ውድ የአንድነት ኃይላት በተለይም የነጻ ሚዲያ አባላትና እንደዚሁም በጣም የማከብራችሁና የማደንቃችሁ የኢሳት ጋዜጠኞች፤ እንደ ማንኛውም ነጻ የዜና አውታር ዜናውን መዘገቡ አግባብ ሲሆን ማህበር ቅዱሳንን አስመልክቶ ትንተናችሁን አቆዩት። የዚህ ማህበር መለያ ባህርዩ ሁሉም ጋር አለሁ ማለቱ ነው። የወያኔ ተልእኮ እየፈጸመ ተቃማዊውን ወገን ደግሞ ማህበሩ እንዳይመታብን እንጂ ከእናንተ ጋር ነኝ ይላል።አንድ ጸሃፊ ስለዚህ እኩይ ማህበር ሁለት ባህሪያት  ሲገልጹ «ጠባያቸው ሁሉ እንደ ሌሊት ወፍ ነው ጥርስም ክንፍም አላቸው» የማህበሩ ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ሙሉጌታ (july 2011)  ለእንቁ ጋዜጣ  በሰጠው ቃለ መጠይቅ አብዛኛው የማህበሩ አባላት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊ እንደሆኑ በይፋ ተናግራል ። ሰለሆነው አሁን ከወያኔ ጋር የተፈጠረው ግጭት የጥቅም እንጂ የዓላማ እንዳልሆኑ ልትገነዘቡ ይገባል። በሌላው መልኩ የሰሞኑ ማቅ የገባበት አጣብቂኝ አቡነ ሳሙኤልን በሚደግፈው በአዜብ የሚመራው ቡድንና የእነ አቦይ ስብሐት ቡድን የሚመራው ቡድን ፍትጊያ አንጸባራቂ ነው። በመሆኑም የዚህን ማህበር ጉዳይ በትንተና መልክ ማጮሁ ለማቅ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ከመሆን አያልፍም። ይልቅ የማህበረ ቅዱሳንን አመራሮች ከአጠቃላይ ጉባኤ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የተማረ ኃይል ይዞ የነበረውን ሀይማኖተ አበው እንዴት እንዳፈረሰ፣በቤተክርቲያኗ ውስጥ ሌላ ማህበር እንዳይቋቋም ማቅ በወያኔ እያታገዘ ያደረገውን ተጽዕኖና የቤተክርስቲያኗ የገቢ ሰነድ ስለማያቀው ንብረትና ገንዘባቸው እስቲ በኢሳት ቀርበው ይናገሩ።

ለማንኛውም አጠቃላይ ጉባኤ መሪዎች በነማን ይመራ እንደነበር፣ ካባውን ቀይሮ ማኅበረ ቅዱሳን በማለት በአዲስ ስምና በጥቂት የንስሃ ልጆቹ እንደተመሰረተ በሚገርም ሁኔታ መንግስት ሲቀየር አቡነ ቴዎፍሎስን የአስተዳደር ተሃድሶ ያሰፍልጋል በሚል አሳልፈው ለገዳይ እንደሰጡ ፓትርያርክ መሮቆሬዎስም አሳልፎ ለመስጠት ያደረጉትን ሙከራ በተጨማሪም ማቅ ከጽዋ ማህበርነት ተነስቶ እንዴት በአንጼ ወደ አደገኛ የቤተክህነት ፈላጭ ቆራጭ ድርጅትነት እንደተለወጠና የተጠቀመባቸውን አካላት የሚያሳይ ጽሁፍ ወደፊት ለማቅረብ እሞክራለሁ።

የአባቶቻችን አምላክ ቤተክርሲቲያናችንና እና ሀገራችንን ይጠብቅ።

ታዬ ብርሃኑ
taye_berhanu@ymail.com
October 2014